# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞክራሲያ ቅጽ** 38 **ቁጥር** 1 **ጥቅምት/ኅዳር** 2004 **ዓ.ም**


## <u>እየሰማ የሞተን እያየ ቅበረው</u>::

ተነግሮት ያልሰማ፣ ተመክሮ ያልተረዳ፣ ተገስጾ ልብ ያልገዛ ምን ጊዜም ቢሆን መዳኛ የለውም:: መከራ ይምከረው ይሆናል ተብሎ ተስፋ ቢደረግም እንኳ፣ መከራውን እየተቀበለ የመከራ ህይወቱን ይኖራታል እንጅ ከመከራው ለመላቀቅ አይሞክርም:: ከመከራ ቀንበር ለመላቀቅ እያንዳንዱ የራሱን ጥረት እስካላደረገ ድረስ ደግሞ፣ ማንም መጥቶ ከመከራው ሊያላቅቀው ከቶ እንደማይችል ያለፉት ሃያ የመከራ ዘመናት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ህያው ምስክሮች ናቸው::

በጭቆና አገዛዝ የሚንገላታ ሕዝብ፣ እያንዳንዱ ዜጋ ራሱን ነፃ ለማውጣት መታገል አለበት ቢባልም እንኳ፣ ለአንድ ዓላማ በኅብረት ተደራጅቶ እስካልተንቀሳቀሰ ድረስ እያረረ ይከስላል እንጅ በነፍስ-ወከፍም ሆነ በተናጠል የሚያደርገው መፍጨርጨር ፍሬያማ አይሆንም:: እንዲያውም፣ በተናጠል ቢፍጨረጨር፣ በጨቋኞቹ መዳፍ ከመደቆስ አያመልጥም:: ይህም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ተደጋግሞ የተከሰተ ሐቅ ነው:: የአምባገነን ሥርዓት አራማጆች ከሚያስደስቷቸው የአገዛዝ ስልቶች አንዱ፣ የሚገዙትን ሕዝብ ራሱን እያታለሉ እንዲኖር ማድረጋቸው ነው:: ለሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ደግሞ፣ ራስን እየደለሉ ከመኖር የበለጠ ተስፋ-ቢስነት ሊኖር አይችልም:: እያረሩ መሳቅ ምናልባት ጊዚያዊ ዕፎይታ ሊሰጥ ይችላል ተብሎ ሊገመት ይችል ይሆናል:: ነገር ግን፣ እያረሩ ማልቅስ ለሰብዓዊ ፍጡር ቀርቶ፣ ለማሽላም አልጠቀመ:: ያም ቢታወቅ ቅሉ፣ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ እያረረ መሳቁ ቢሰለቸው፣ እያለቀሰ የመከራ ሕይወቱን ከመግፋት አልተላቀቀም:: ይህንን ለማድረግ ደግሞ ማንም አይከለክለውም:: ይልቁንም፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ መከራና ለቅሶ የሚደሰቱ ጥቂቶች አይደሉም:: የኢትዮጵያን ሕዝብ የደም ዕንባ የሚያደርቅ ወቅትና ኃይል እንደሚመጣ ግን አንዳችም ብዥታ የለንም::

የሚገዙትን ሕዝብ ከፋፍሎ መጨቆን የአምባገነኖችና የቅኝ ገዥዎች የቆየ ብልሃት መሆኑ ቢታወቅም፤ የወያኔ ዘረኛ ገዥዎች ግን፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር፣ በሃይማኖትና በቋንቋ ለመከፋፈል የሞከሩት እኩይ ጥረት ፈጽሞ አልያዘላቸውም:: ለዚህም ዓቢይ ምክንያት፣ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለከፋፋዮችና ለዘረኞች ዕኩይ ዕቅድ ቦታ ሳይሰጠው በመቅረቱ ነው:: ይህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅነት በታሪክ ተደጋግሞ የተረጋገጠና የተመዘገበ ሆኗል:: የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ወኪሎች፣ እነዱካ ዲ አውስታ፣ ጀኔራል ዲቦኖ እና ሌሎቹም የቅኝ ግዛት አስተዳደራቸውን በስድስት ግዛተ-ክልል መድበው፣ ኤሪትሪያ፣ ሶማሊያ፣ አማራ፣ ሐረር፣ ሸዋና ኦሮሞ-ሲዳሞ በሚል ከፋፍለው፣ ጥንታዊቷን ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፣ ዜጎቿንም እንደ ሕዝብ ከታሪክ መዝገብ ለመፋቅ ሞክረው ነበር:: ይህ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለማጥፋት የተደረገው የኮሎኒያሊስቶች ዕቅድ ግን፣ በኢትዮጵያ አርበኞች የተባበረ ትግል ሳይሳካ ቀርቷል:: የቤኒቶ ሙሶሊኒ የጦር መመሪያም፣ ሁሉንም ጨርስና ብቻህን ተመለስ (አማሳቶ ቱቲ ሪቶርኖ ሶሎ) ከድንፋታ አላለፈም:: ኮሎኒያሊስቶች የቻሉትን ያህል ሕዝብ ቢጨፈጭፉም፣ የኢትዮጵያ ትንሣዔ ግን በጀግኖች መሥዋዕት ዕውን ሆኗል:: ዛሬም የሚሆነው ይህ ነው::

የወያኔ ጎሰኞችም የጎሳ ካርታ መጫወቻቸው እየወየበ መጥቶባቸዋል:: ይህ የከሸፈ ዘዴያቸው እንዳልያዘላቸው ሳይገነዘቡት እንዳልቀሩም እየታየ ነው:: ታዲያ ዛሬ ያመጡት ዘዴ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ እያደኸዩና እያቆራመዱ ለመግዛት አዲስ ብልሃት ማምጣታቸው ነው:: ሰሞኑን ያወጡት የከተማ ቦታ ባለቤትነትን ወደሊዝ የመቀየር አዋጅ፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ፣ የራሱን የመኖሪያ ቤት በሊዝ እየተሸለገ እንዲማቅቅ ለማድረግ ታስቦ የተጠነሰሰ እኩይ ዕቅድ ነው:: ለአለፉት ሃያ ዓመታት ከፋፍሎ ለመግዛት የሞከሩት ዕቅድ እንዳልያዘላቸው ስለተገነዘቡ፣

"እያደኸየህና እያደነቆርክ ግዛ" የሚል ፈሊጣቸውን በአዲስ ፋሽስታዊ ፖሊሲ ለመፈተሽ በመሞከር ላይ ናቸው:: ለፍቶ-ጥሮ-ግሮ የሠራውን የራሱን አንጡራ የመኖሪያ ቤት በሊዝ ይዞታ ሥር እያስገደዱ፣ በዕለት-ተዕለት ችግሩ ብቻ እንዲብተከተክ አድርገው ስለ ሀገሩና ነፃነቱ እንዳያስብ ለማድረግ ያቀዱት ተንኮል መሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ተረድቶታል:: በመሆኑም፣ አዋጁን አምርሮ በመቃወሙ ፖሊሲያቸውን ወደ ተግባር ለመተርጎም አሁን እየተውገረገሩ ይገኛሉ:: የሕዝቡን የተቃውሞ ግለት ካቀዘቀዙ በኋላም በልዩ የውስጥ መመሪያ ዕቅዳቸውን እንደገና ለመተግበር ወደኋላ እንደማይሉ ግን ተደርሶበታል:: በወያኔዎቹ ቤት፣ ያለ እነርሱ በስተቀር ሌላው ሁሉ የማያስብና የማይመራመር ይመስላቸዋል:: ይህም ከንቱነት የመጣው፣ "የኢትዮጵያን ሕዝብ ልብ ደህና አድርገን አውቀነዋልና የትም ሊደርስ አይችልም" ከሚል ከትንሽነት የመነጨ ትዕቢት ለመሆኑ ከማንም ኢትዮጵያዊ የተሰወረ ሊሆን አይችልም::

ሰሞኑን ወያኔዎቹ ያወጡት የከተማ ቦታንና የዜጎችን የግል መኖሪያ በሊዝ ፖሊሲ ውስጥ የማስገባት አዋጅ፣ እንዲሁ በደፈናው/በተናጠል ሊታይ የሚገባው ውሳኔ አይደለም:: የአንድ ብቸኛ ፓርቲ አምባገነንን ሥልጣን በሁለንተናዊው ረድፍ የበለጠ ለማጠናከር ታስቦ የተዘጋጀ ስልት ነው:: ይህም ወያኔ ብቻውን ተጠናክሮ እንዲወጣ፣ ተቃዋሚዎቹን ሁሉ ቢቻል ለማጥፋት፣ ያ ካልተሳካ ደግሞ፣ ሳያፈናፍን ለመቆጣጠር የሚያስችለውን የአገዛዝ ስልት በመሸረብ እንደቆየው ሁሉ፣ ተጨማሪ ቆላፊ መረብ ለመዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል::

ይዋል ይደር እንጅ፣ በሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ የተቀጣጠለው የሕዝብ አመፅ ወያኔዎቹን እንደሚለበልባቸው ማንም ሳይነግራቸው እራሳቸው ያውቁታል:: አምባገነኖች አንድ በአንድ በየተራቸው ሕዝባዊና ታሪካዊ ፍርድ እያገኙ በሚሄዱበት በአሁኑ ወቅት፣ የወያኔ መሪዎች ለመውሰድ የመረጡት እርምጃ፣ ሥልጣናቸውን በሰላም ለሕዝብ ማስረከብ ሳይሆን፣ ጊዜያቸውን ለማራዘም የሚያስችላቸውን ከንቱ ዕቅድ መንደፍ ሆኖ አግኝተውታል:: በመሆኑም ከዚህ የሊዝ ፖሊሲ ጋር፣ ከቻይና አለቆቻቸው የተሰጣቸውን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ፣ የአንድ ብቸኛ አምባገነን ገዥ ፓርቲ ፍጹማዊ ሥልጣንና ኃይል ማረጋገጥ መቻል እንደሆነ አምነውበታል:: ለዚህ ማረጋገጫ ዋስትና ለመስጠት <u>የልማት ሠራዊት መረብ (ኔት ዎርክ)</u> የሚል መመሪያ አውጥተዋል:: ይህም እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ በቅርብ ለመቆጣጠር የታቀደ የማስፈፀሚያ ስልት ነው:: ይህ ሰፊ መረብ፣ ቤተሰብን መንደርን፣ ጎጥን፣ ትምህርት ቤትን፣ የሥራ ቦታን፣ ...ወዘተ ለመቆጣጠር እንዲያስችላቸው ሆኖ፣ በአምስት አምስት ሰው እየተደራጀ፣ የያንዳንዱን የከተማ ነዋሪ እንቅስቃሴ በመከታተል ለበላይ አለቆቹ ሪፖርት የሚያደርግ (ዘገባ የሚያቀርብ) ሆኖ ተደራጅቷል:: ማንኛውንም መረጃ ለወያኔ ባለሥልጣናት በየዕለቱ የማቅረብ ግዴታና ተግባር እንዳለበት በዚህ መረብ ውስጥ ገብቶ የሚንቀሳቀሰው የወያኔ ወኪል ጥብቅ መመሪያ ከመሃላ ጋር ታድሎታል:: ይህም ዕቅድ ለአሁኑ ሥልጣናቸው መከላከያ እንዲጠቅማቸው ተብሎ የወጣ ብቻ ሳይሆን፣ ለሚቀጥለው የወያኔ ምርጫ፣ የራሳቸውን ሰዎች በይበልጥ ለማደራጀትና ለማዘጋጀትም ጭምር ነው - ለምርጫ ቲያትሩ መተወኛ እንዲሆነው እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም::

ከምኒልክ ግቢ የምንወጣው ሬሳችን እየተጎተተ እንጅ በህይወትማ አይሞከርም የሚል አቋም ያላቸው ግለሰቦች በመሆናቸው፣ በሥልጣን ኮርቻ ተፈናጦ ለመቆየት በየጊዜው አዳዲስ እኩይ ዕቅድ ማውጣታቸውን ይቀጥሉበታል:: በሰሜን አፍሪካ የነበሩት አምባገነን መሪዎች አንድ ባንድ በሕዝባዊ አመፅ እየተደመሰሱ መጥፋታቸውን ቢመለከቱም እንኳ፣ የወያኔ መሪዎች፣ በእነርሱ ላይ እንደማይከሰት፣ ራስን ከመደለል በመነጨ ግብዝነት ምክንያት፣ ለማመን ይፈልጋሉ:: ለዚህ የግብዝነት ዕምነታቸው አራት ምርኩዞች እንዳሏቸው ያስባሉ:: አንደኛው፣ ጦሩን፣ ፀጥታውንና መረጃውን ሌሎቹንም የመጨቆኛ መሣሪያዎች በሙሉ ስለተቆጣጠሩ፤ ሁለተኛው፣ የተቃዋሚውን ኃይል ሁሉ ከፋፍለንና አዳክመን በመዳፋችን ሥር አድርገነዋል ብለው በማመናቸው፤ ሦስተኛ፣ የሀገሪቱን የንግድ፣ የገንዘብ፣ የኤኮኖሚና ሌሎቹም ብሔራዊ ሀብቶች በሙሉ በእጃችን ውስጥ ገብተዋል ብለው ስለሚያምኑ፤ አራተኛ፣ ምዕራባውያን አለቆቻቸውና ሌሎች ተባባሪዎቻቸው ያልተቆጠበና ያልተቋረጠ ሁለንተናዊ ርዳታ መለገሳቸውን ይቀጥሉልናል ብለው ስለሚያስቡ ነው::

በላይኛው አንቀጽ የተዘረዘሩት አራት የወያኔ ምርኩዞች ግን አንድ በአንድ ሲፈተሹ ፣ እነዚህን የጎሰኛ ቡድን አባላት ከማይቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ ሊያድኗቸው ከቶ አይችሉም:: ሁሉም አንድ በአንድ እንደጉም ተንነው እንደሚጠፉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዕርግጠኝነት ማመን ይችላል:: ጦሩን፣ ፀጥታውንና የመጨቆኛ መሣሪያዎቹን ሁሉ እስከመጨረሻው ድረስ ተቆጣጥረናል እና ማንም አይደፍረንም ማለት፣ የአንድን ኅብረተሰብ የሥነ-አዕምሮ ምንነት ጠንቅቆ ካለመረዳት የመነጨ ከንቱነት ብቻ ሳይሆን፣ የታሪክን ትምህርት ካለመከታተል የመነጨ ድንቁርናም ጭምር

ነው። ሠራዊቱና የፀጥታው ሠራተኞች ሁሉ ከሀገሪቱ ዜጎች የመጡ በመሆናቸው የኋላ-ኋላ ከምልዕተ-ሕዝቡ ጎን በመቆም የወያኔን መሪዎች እርቃነ-ሥጋቸውን በማስቀረት ሚናቸውን እንደሚለዩ፣ የታሪክ ማስረጃ እየጠቀሱ መናገር ይቻላል። "ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ለዘለዓለም ይኑሩ!" ሲል የነበረው ሁሉ፣ በየካቲት ስድሳ ስድስት አብዮታዊ ነበልባል በመደናገጥ፣ ሰልፉን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ማስተካከሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቅርብ ትዝታው ነው። በተለይማ የወያኔ ጆሮ-ጠቢዎችና ሰላዮች ሁሉ፣ ከሞያቸው በሚያገኙት መረጃና የውስጥ ምሥጢር በኩል፣ ሁለ-መናው እንዳልሆነ ሆኖ ሲያገኙት፣ እራሳቸውን ለአዲሱ ሁኔታ ለአገልግሎት ለማቅረብ ስለሚዘጋጁ ቆዳቸውን ከሰውነታቸው ላይ ለመገልበጥ በሚያስገርም ፍጥነት እንደሚሽቀዳደሙ የታወቀ ነው። ስለዚህ፣ የወያኔ መሪዎች የመከላከያ ሠራዊቱንና የፀጥታውን ክፍል ተቆጣጥረነዋልና የሚነካን የለም ማለታቸው የቢከፍቱት ተልባ መተማመን ሆኖ ይቀራል። የኢኮኖሚ አውታሮችና የሀገሪቱም የሀብት ምንጭ ሁሉ በእጃችን-በደጃችን ስለሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ እያደኸየን ቅስሙን በመስበር ፀጥ-ለጥ አድርገን ለብዙ ጊዜ እንገዛዋለን የሚለው ምኞታቸውም ከሞራል ሽንገላ የሚዘል አይሆንም። ምናልባት የሀገሪቱን ባንኮች፣ የንግድና የገንዘብ ተቋማትን መቆጣጠራቸው፣ ሀብት ንብረት እየዘረፉ ወደ ውጭ ለማሸሽ ያስችላቸው እንደሆነ እንጅ በዘለቄታው የኢትዮጵያን ሕዝብ እየገዙ ለመኖር የሚያስችላቸው ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም፣ የሀገርን ብሔራዊ ሃብት በመቆጣጠር ከሕዝባዊ አመፅ ለመዳን የሚቻል ቢሆንማ ኖሮ፣ ከኢራኑ ሻኽ መሀመድ ባሕላቢ የበለጠ ሀብት የተቆጣጠረና ያከማቸ አልነበረም። በአካባቢው ተወዳደሪ ያልነበረው ሳባክ የተሰኘው ኃይለኛው የፀጥታ ተቋሙም ሻኹን ከማይቀረው ውድቀቱ አላተረፈውም። ተጨማሪ የታሪክ ማስረጃ ካስፈለገ ደግሞ፣ የዛይሩን ሞቡቱ ሴሴ ሴኮን የመጨረሻ ውድቀት መጥቀሱ ይበቃል። ምዕራባውያን እንደፈረስ ሲጋልቡት ከቆዩ በኋላ፣ ቀን ሲጥለው፣ የኅክምና እርዳታ እንኳን እንዲያገኝ ርኅራኄ አላሳዩትም።

የተቃዋሚው ክፍል የተከፋፈለና የተወናበደ በመሆኑ፣ እኛን አያሰጋንም ማለታቸው፣ ከዕውነት የራቀ አባባል አይደለም ቢባልም፣ ለጊዜው የኢትዮጵያን ሕዝብ ያሳዘነ ሁኔታ ነው ለማለት ቢያስችልም፣ የኃይሎች አሰላለፍ ከመቅጽበት ተለውጦ የተቃዋሚው ጎራ አርዕድ-አንቀጥቅጥ ኃይል እንደሚሆን፣ የሀገሪቱ ጠላቶችና ወያኔዎች ለማመን ባይፈልጉም፣ ይህ ሐቅ ግን የማይቀር ታሪካዊ ክስተት ነው። ከአንዳንድ የምዕራባውያን ሀገሮች በሚያገኙት እርዳታና ትብብር ተማምነው፣ ወያኔዎች ኢትዮጵያን ለብዙ ጊዜ ለመግዛት መሠረት ያደረጉት ማጠየቂያቸው እንደዚሁ ብዙ ምዕራፍ ሊያስኬዳቸው የሚያስችል አይደለም። ምክንያቱም፣ ሁል ጊዜ የውጭ እርዳታና ትብብር የሚመሠረተው "እርዳታ" በሚያደርገው ሀገር ወቅታዊ ጥቅም ላይ በመሆኑ፣ የሁኔታዎቹ ሁለንተናዊ ለውጥ በሚከሰትበት ጊዜ ወያኔ ሲቸርለት የነበረው እርዳታ ሁሉ ዕፍ ሲሉት ጭልጥ ሆኖ ይቀራል። ከዚህም በቀር፣ የየሀገሮቹ ተዛምዶና የዓለም-አቀፉ ዲፕሎማሲ የዘወትር ትኩረቱ፣ በእከክልኝ-ልከክልህ፣ የሽማኔ መወርወሪያ ቅኝት ዙሪያ በመሆኑ፣ ሁኔታው ሲለወጥ፣ የወያኔ አለቆችና ተባባሪዎች፣ ወያኔን እንደ ዋንጫ መቀመጫ አውልቀው እንደሚጥሉት ብዙ ማስረጃ መጥቀስ አያስፈልገንም። ካስፈለገም፣ ምዕራባውያን፣ በነባር ታማኞቻቸው፣ በቱኒዚያው ቤን ዓሊና በግብፁ ሆስኒ ሙባረክ ላይ በቅርቡ የፈፀሙትን ድርጊት ጠቅሶ ማለፉ ይበቃል።

ምዕራባውያን ጥቅማቸውን ሊያስጠብቅላቸው የሚችለውን አዲስ ታማኝ አገልጋይ በመፈለግ ሂደት ውስጥ መሆናቸውን ብንገነዘብም፣ ለጊዜው ግን ከወያኔ የበለጠ ታማኝ አገልጋይ እንደሌላቸው እያመነቱም ቢሆን ይረዱታል። ያም ቢሆን ቅሉ፣ የሀገሪቱን ውስጠ-ምሥጢር በዝርዝር የማወቅ ዕድል በማግኘታቸው፣ የሕዝባዊው አመፅ እየጎላ በሚመጣበት ወቅት አዲስ ታማኞችን መልምሎ ለማዘጋጀት የሚያስችላቸውን እርምጃ ከመውሰድ ወደ ኋላ እንደማይሉ ይገመታል። በመሆኑም፣ ምናልባት በአዲስ ጉልበትና ታማኝነት የሚጋልቡትን አገልጋይ ፈረስ አሰልጥኖ ከማዘጋጀት ወደ ኋላ የሚሉ አይሁንም። በሚያዘጋጇቸው ታማኝ አገልጋዮቻቸው አማካኝነትም፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከዓ-ምድር ውስጥ በሚከሰተው ክፍተት የይስሙላ-ጥገናዊ ለውጥ በማድረግ ይዞታቸውን ለማረጋገጥና ዕቅዳቸውንም ለማስፈፀም ጥረት ያደርጋሉ። በሀገሪቱ የፖለቲካ ምህዳርም ለውጦች እንደተፈጠሩ በማስመሰል፣ የሕዝቡን ስትራተጅያዊ ራዕይና የትግሉንም ሂደት አቅጣጫ ለማስለውጥ ይጥራሉ። ለዚህ ሁሉ ጥረታቸው እንደማጠየቂያ ሊጠቀሙበት የሚፈልጉት፣ እንዳለፈው ጊዜ ስለ ዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች መከበር የውዳሴ ከንቱ ምንባብ በማሰማት ይሆናል። ይህ ሁሉ የተቀነባበረ የውስጥና የውጭ ደባ ምን ጊዜም ቢሆን ከሕዝባችን አዕምሮ የተሰወረ አይደለም። የዛሬ ሃያ ዓመት ገደማ ወያኔን በሥልጣን ላይ ሲያስቀምጡም "ዴሞክራሲን ካላመጣችሁ እርዳታ አንሰጣችሁም" በማለት የሕዝቡን ተቃውሞ ሊያለዝቡላቸው እንደጣሩ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አዕምሮ ውስጥ የሚፋቅ አልሆነም። በዘመነ-ወያኔ፣ ዕልፍ-ዓዕላፍ ዜጋ

ተጨፍጭፎ፣ ቁጥር-ስፍሩ የማይታወቅ ሰው መዳረሻው ጠፍቶ፣ በዕንበለ-ፍርድ ቁጥሩና ልኩ ያልተደረሰበት ዜጋ በየወኅኒዎች ታጉሮ፣ ይህ ነው የማይባል ዜጋ በየአቅጣጫው ከሀገሩ መሰደዱ እየታወቀ፣ ምዕራባውያን አሁንም ለወያኔ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ይሰጡታል። የራሳቸው ዓላማ እስከተፈፀመ ድረስ፣ የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች መከበር አለመከበር ለእነርሱ ደንታ እንደማይሰጣቸው፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የበለጠ ሊገነዘበው የሚችል የለም።

አንዳንድ ወገኖች ይህንን ሁሉ በአሁኑ ወቅት መዘርዘር አስፈላጊ እንዳልሆነና እንዲያውም የወቅቱን የዲፕሎማሲ ፈሊጥ ያላገናዘበና ጮሌነትም የጎደለው እንደሆነ ሊቆጥሩት ይችሉ ይሆናል። "**ኀልም እንደፈቺው**" ነውና፣ ምናልባትም ይህ አስተሳሰብ፣ የየራሳቸውን ኀልም ሊያስተጋባላቸው ይችላል። ነገር ግን ዛሬ፣ የሀገራችንና የዜጎቿ ቅድሚያና ትኩረት የኢትዮጵያ መዳን አለመዳን፣ እንደ ሀገር መቀጠል አለመቀጠል እንጅ፣ የዲፕሎማሲ ፈሊጥና ከየሀገሮች ጋር የሚኖረው ተቃርኖ ወይም ዝምድና አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ወቅታዊው ጥያቄ፣ የሀገሩ መዳን፤ የዴሞክራሲ መስፈንና የዜጎቿ አንድነት ነው።

በተለይ ለኢሕአፓ፣ የአፈጣጠሩ መሠረት፣ የዕድገቱና የትግሉ ሂደት፣ እንዲሁም፣ የራዕዩና የተስፋው አልፋ-ኦሜጋ የኢትዮጵያን ብሔራዊ፣ ዋናና ዘላቂ ጥቅም፣ የዜጎቿንም ነፃነት፣ ሉዓላዊነትና ብልፅግና እንዲሁም የዴሞክራሲ ሥርዓትን ማስፈንና ማስከበር በመሆኑ፣ ይኽንን ዕውን ለማድረግ በሚያደርገው ትግል፣ ወደ "ሥልጣን እንድወጣ ማን ይተባበረኛል? ማንስ ይረዳኛል?" የሚሉት ጥያቄዎች በቅድሚያና በዋናነት አስጨንቀውትም አያውቁ። ይህም የሆነበት ዓበይት ምክንያት፣ የፖለቲካ ሥልጣን ምንጭ (ሕዝቡ እንደመሆኑ)፣ በዴሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ በሚካሄድ የሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ የሚፈጸም መሆኑን ኢሕአፓ አጥብቆ በማመኑ ነው። ለዚህም ነው፣ ፓርቲው እስካሁን ድረስ፣ በተመሠረተባቸው ዓላማዎችና በቃል-ኪዳን በተገነቡ የመርኅ አቋሞቹ ላይ ሊደራደር ፈቃደኛ ያልሆነው። ይህም በመሆኑ ከፋፋይና ተገንጣይ ክፍሎች ሁሉ "ዓባይ ኢትዮጵያ" እያሉ ሲፎትቱት እንደነበር የቅርብ ትዝታ ነው። ለፓርቲው ግን፣ "**ታላቋ ኢትዮጵያ** " የሚል ስም በማግኘቱ ሲኮራበት ኖሯል። ይኖራልም። የፓርቲው አባላት፣ ዓይነተኛ ራዕያቸው፣ ዓላማቸውን ሸጠው፣ በሆነው ዘዴ ሥልጣን መያዝ ቢሆንማ ኖሮ፣ ከወያኔ በፊት ከምኒልክ ግቢ መግባት እንደሚችሉ ያውቁት ነበር። ኢሕአፓ "ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት" የሚለውንና፣ ከሱዳን ጋር ተባብሮ የኢትዮጵያን ግዛት ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት የመስማማቱን ጎዳና አለመያዙ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው። በኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት ከመደራደራቸው በፊት ኢሕአፓና አባላቱ የራሳቸውን መጥፋት ይመርጣሉ። ይህ አቋማቸው ለነርሱ የተከበረ-የተቀደሰ ነው። በጊዜና በቦታ የማይወሰን፣ በትግል መርዘምና በመሥዋዕት መራራነት የማይወይብ ፣ ከየትኛውም አቅጣጫ በሚሰነዘር ጫናም ሆነ ተፅዕኖ ፍንክች የማይባልበት አይበገሬ ባኅርይና አቋም መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ የፓርቲው ባላንጣዎች ሁሉ የማይክዱት ሐቅ ነው። መንግሥቱ ኃይለማርያምም ሆነ ምድረ-አስገንጣይ መንጋ ሁሉ እንደ እንቆቆ እየጎመዘዘውም ቢሆን፣ ይህንን ሐቅ ይቀበለዋል።

ይህ በየአካባቢው የተቀጣጠለው ፀረ-አምባገነን ዓመፅ፣ በሀገራችን መቸ እና እንዴትስ እንደሚጀመር፣ ወቅቱንና ሁኔታውን በትክክል ለመተንበይና ለመናገር ባይቻልም አይመጣም አይከሰትም የሚል የተስፋ መቁረጥና የማመንታት ሁኔታ እንዲኖር ከወያኔ ፕሮፓጋንዳ አገልግሎት አካባቢ እንዲናፈስ ቢሞከርም፣ ታሪካዊው ሐቅና ነባራዊው ሁኔታ ግን ዳግማዊው የካቲት ስድሳ ስድስት ሕዝባዊ አመፅ በኢትዮጵያ አድማስ እያንዣበበ መሆኑን ያመለክታል። ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ ደግሞ፣ አምባገነን ሥርዓትን እንደሚደመስስ በዕርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ምክንያቱም ሕዝባዊ አመፅ ሲቀጣጠል፣ ማንም ምድራዊ ኃይል ሊያቆመው ቀርቶ፣ ሊገታው የማይችል መሆኑ ስለሚታወቅ ነው። ይህ ዳግማዊው ስድሳ ስድት የካቲት አመፅ፣ የሕዝቡን ነበልባላዊ ቁጣ አዝሎ የሚመጣው፣ በሀገራችን ውስጥ ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎች እየተሟሉና እየተስተካከሉ ሲመጡ ነው። እነርሱም፣ በአሁኑ ወቅት እየተሟሉ በመምጣት ላይ ይገኛሉ።

"የመጨረሻዋ ገለባ የግመሉን ጀርባ ትሰብራለች" እንዲሉ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመከራ ፅዋ ሞልቶ ሲገነፍል፣ የአመፁ ግለት የመጨረሻውን ምዕራፍ መያዙ አይቀሬ ነው። የገዥው ፓርቲ መሪዎችና የመጨቆኛ መሳሪያዎቻቸው፣ የአመጹን መምጣትና መስፋፋት ለማስቀረት ባይቻላቸውም፣ ሂደቱን ለማዘግየት፣ ፍጥነቱን ለመቀነስም ሆነ፣ ጊዜውንም ለማስተላለፍ ይፍጨረጨራሉ። ወያኔዎቹ ዛሬ የሚያደርጉትም ይኽንኑ ነው። ከጥረቶቻቸው ሁሉ ቅድሚያ የሚሰጧቸው፣ የአደጋ መከላከያ ምሽጋቸውን ማጠናከርና በአዋጅና ግድብ ግንባታ ጋጋታ ሕዝብን ለማደናገር የሚያደርጓቸው

ሙከራዎች ናቸው:: ይኽንን ወቅታዊ ድርጊት ለመፈፀም የሚያስገድዳቸውም፣ የቆሰለ አውሬ ባኅርያቸው ለመሆኑ ሁሉም ዜጋ ደርሶበታል:: የቆሰለ አውሬ፣ ዛፉና ቅጠሉ ሁሉ ጠላቱ ስለሚመስለው፣ ተጨንቆና ተጠብቦ የሚሠራውንና የሚያደርገውን ያሳጣዋል:: ለዚህም እኮ ነው በማክተሚያ ዘመናቸው፣ አምባገነኖች ሁሉ፣ የመመከሪያና ከሕዝብ ጋርም የመታረቂያ ጊዜያቸውን በከንቱ በማሳለፋቸው፣ **እየሰሙ መሞታቸው ብቻ ሳይሆን፣ እያዩም የሚቀበሩት**::

በሌላ በኩል ግን እዚህ ደረጃ መድረሳቸው የማይጠበቅ ክስተት አይደለም:: ለምን ቢባል፣ በጭቆና አገዛዛቸው ዘመን፣ ከባድና አሰቃቂ የሆነ ብሔራዊ ወንጀል በመፈፀማቸው፣ ወንጀለኛው አዕምሯቸው የሰከነ ኅሊና ሰጥቷቸው፣ ከሕዝብ ጋር ለመታረቅ የሚያስችል አቅል ስለማያገኙ ነው:: ለዚህ ሐቅ የሩቅ ታሪክ ማስረጃ ፈልጎ መጥቀስ አያስፈልገንም:: በዚህ ወር መግቢያ ላይ የሊቢያ ሕዝብ አመፅ የወሰደውን እርምጃ መጥቀሱ ይበቃል:: መሪያቸውን ዓይኑ እያየ ሲቀብሩት፣ ሌላው ቀርቶ፣ አረቦች ነን፤ ዘመዶችህ ነን ሲሉት የነበሩት የወያኔ መሪዎች ሊያድኑት ቀርቶ የአዞ እንባ እንኳ አላነቡለትም:: ለካ፣ "ኢትዮጵያን እናጠፋለን የሚሉ ሁሉ፣ እነርሱ ይጠፏታል እንጅ፣ ኢትዮጵያስ አትጠፋም" የሚባለው በታሪክ ማስረጃ የሚደገፍ ሐቅ ነው!

አሁን ተወደደም ተጠላ ፣ በኢትዮጵያ ሀገራችን የፖለቲካ መልከ-ምድር ያለው ተጨባጩና አቅጣጫ ጠቋሚው የሚያመለክተው የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ ህይወትም ሆነ የሰላሙና የዜጎች ደኅንነት ጉዳይ፣ ከቁጥጥር ውጭ እየሄደ መሆኑን ያረጋግጣል:: ለነዋሪዎቹም የህይወት ዋስትና ማንም ኃይል ኃላፊነት ሊወስድ ከማይቻልበት ደረጃ መድረሱን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች በመፈጠር ላይ ናቸው:: ዜጎች የኑሯቸው ሁኔታ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ የዋጋ ውድነት ምክንያት በቀን አንድ ጊዜ እንኳ ጠግቦ መብላት አልተቻላቸውም:: የሀገሪቱ ገንዘብ ዕቃ የመግዛት አቅሙ እጅግ ሲበዛ እየደከመ መምጣቱ ብቻ ሳይሆን፣ የዋጋ ግሽበቱን ፍጥነት ሊያቆመው የሚችል ሁኔታ የለም:: የሀገራችንን ሁለንተናዊ ሁኔታ በዝርዝር ለማወቅ ካስፈለገ ፣ ሰሞኑን የዓለም ሀገሮችን የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የኑሮ ደረጃ በቅርብ የሚከታተለው የዓለም አቀፍ ተቋም የመዘገበውን ዓመታዊ ዘገባ መመልከቱ ብቻ ይበቃል:: የሀገራችን ሁለንተናዊ ችግር፣ በቀጥታ ከሚመለከታቸው ከራሳቸው ከዜጎቿ አልፎ-ተርፎ፣ ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ አያሌ ተቋማትን እያነጋገረና የችግሩም ስፋትና ክፋት የአደባባይ ምሥጢር መሆኑ እየታወቀ የወያኔ መሪዎች፣ ዓይናችንን-ግንባር ያድርገው በማለት የኢትዮጵያን ሕዝብ ማታለላቸውን ቀጥለውበታል:: ባለፈው መስከረም ወር፣ የወያኔ መሪዎች፣ ፓርላማችን በሚሉት ቦታ በመገኘት፣ ባደረጉት ንግግር፣ በእነርሱ ዘመን በኢትዮጵያ ማርና ወተት እንደሚዘንብ ለማስረዳት ሞክረዋል:: ይህን ፕሮፓጋንዳቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢያሾፍበትም፣ ሲያስነጥሳቸው፣ መሃረብ ለማቅረብ የሚሽቀዳደሙት የፓርላማቸው አባላት ግን ንግግራቸውን አጨብጭበው ተቀብለውታል። የሂትለር የናዚ ፓርቲ፣ "ጀርመንን አንድ ሽህ ዓመት እገዛለሁ!" ሲል የነበረው ፕሮፓጋንዳ፣ የዶግ-አመድ ሆኖ እንደቀረ ስለምናውቅ፣ የወያኔ መሪዎች ድንፋታና ፉከራም እንደዚሁ ወደማይቀርለት ከርሰ-መቃብሩ እንደሚወርድ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይጠራጠርም:: "የአንድ መቶ ዓመት ብቻ ታሪክ ያላትን ሀገር አንድ መቶ ዓመት እንገዛለን" የሚለው የወያኔ መሪዎች ዕቅድን በማክሸፍ፣ የአያሌ ሽህ ዘመናት ታሪክ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሩን ከአፍራሾች መዳፍ አውጥቶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እንደሚመሠርትም በፅናት ያምንበታል::

ኢሕአፓም፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ማህፀን የወጣ በመሆኑ፣ ዓላማውና ራዕዩ ከህገሩ ሕዝብ ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል ነው:: በመሆኑም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ራዕይ ዕውን እስከሚሆን ትግሉን ይቀጥላል:: የሀገራችንን ሁለንተናዊ ችግሮች ለማስወገድ የሁሉንም ዜጋ የተባበረ ትግል ስለሚያስፈልግም፣ ይህን ታሪካዊ ግዳጅ ለመቀበል ሕዝብና የአንድነት ኃይሎች ሁሉ መነሳት መታገል አለባቸው::

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች!!
ድል የሕዝብ ነው!!
እናቸንፋለን!!